ባሮች የሚያነጉበት አንድም ቀን የለም ሁለት መልዐክ ወርደው እንዲህ የሚሉበት ቢሆን እንጂ፤ አንደኛቸው: "አላህ ሆይ! ለሰጪ ምትኩን ስጠው!" ሲል ሌላኛቸው ደግሞ "አላህ ሆይ! ለቋጣሪ ጥፋትን ስጠው!" ይላል።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው : ነቢዩ (ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም)
የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: «ባሮች የሚያነጉበት አንድም ቀን የለም ሁለት መልዐክ ወርደው
እንዲህ የሚሉበት ቢሆን እንጂ፤ አንደኛቸው: "አላህ ሆይ! ለሰጪ ምትኩን ስጠው!" ሲል ሌላኛቸው ደግሞ "አላህ ሆይ! ለቋጣሪ ጥፋትን ስጠው!" ይላል።»
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ፀሐይ በምትወጣበት ቀናት ሁሉ ሁለት መልአኮች ወርደው እንደሚጣሩ ተናገሩ። አንደኛቸው እንዲህ ይላል: አላህ ሆይ! አላህን ለመታዘዝ፣ ለቤተሰቦቹ፣ ለእንግዶቹ፣ ለበጎ አድራጎት ለሚሰጥ ሰው ምትኩን ስጠው፤ ካወጠው የተሻለ ተካለትም ባርክለትም። ሌላኛው ደግሞ "አላህ ሆይ! ከመስጠት የሚቋጥርን ጥፋትን ስጠው፤ ለሚገባቸው ከመስጠት ገንዘቡን የነፈገንም ገንዘቡን አውድምበት!" ይላል።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/3379